# ሁለት የ ካቲቶች

መንግስቱ ሙሴ

ፌብሯሪ **19 2016**

ሁለቱ የካቲቶች በኢትዮጵያ ታሪክ መሰረታዊ ለውጦች በህዝባችን አስተሳሰብ አስቀምጠው አልፈዋል። ሁለቱ የካቲቶች በ 37 አመታት ልዩነት የተከናወኑ የታሪክ ቀናት ናቸው። የመጀመሪያው ከኋለኛው በእድጉ ሲለይ የሁለተኛው ከመጀመሪያው የሚለየው የህዝብ በእገር ወለድነቱ ነው። በተረፈ ሁለቱም የካቲቶች በህዝብ አስተሳሰብ (consciousness) ከፍተኛ ለውጥ በማምጣት ለትውልድ የታሪክ ማህተም ሰጥተውን አልፈዋል። የካቲት 1966 እንደሚታወቀው ጥንታዊውና ንጉሳዊ ስርአት በህዝባዊ አብዮት የተፈነቀለበት ነበር።

መቸም ግታዊ ያልተቀነባበሩ አብዮቶች ሕዝብ የተነሳለትንና ያሰበውን ሳይሆን የተደርጀ ብዙውን ግዜም ትጥቅ ያለው የሚነጥቀው ለመሆኑ ከእኛ ታሪክ ባሻገር በሳለፍናቸው የቅርብ አመታት በሰሜን አፍሪካ የተነሱ ህዝባዊ አብዮቶች የደረሰባቸውን የባሰ አደጋ መገንዘብ ይቻላል። የህዝብ ንቃትና ዝግጁነት ከድርጅታዊ ጥንካሬ ጋር ተገጣጥሞ ያለመገኘት አደጋም በባሰ ጨቋኝ እን አፋኝ የመያዙ ጉዳይ ነው። እናም የካቲት 1966 ህዝብ ስርአትን በአብዮት ቢቀይርም የተደራጀው ወታደራዊ ሀይል የውጤቱ ተጠቃሚ በመሆን በቀጣይ አመታት "ነጻ እርምጃ" "ቀይ ሽብር" በተባሉ ህግ አልባ መንግስታዊ ወንጀሎች ትውልድ ጠፍቷል። የሁለት የካቲቶች ውጤትና ታሪካዊነትንም በዚህ አይነት እንመለከተዋለን።

የካቲት 12 1929 ዓም የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥቷል። ህዝብ ከጠላቱ ምንም አይነት ይቅርታን እንደማይጠብቅ። ታግሎ ከማስወገድ ውጭ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን ያች ቀን በማስተማሯ የፋሽት ወራሪ የመጨረሻዋ ቀን ብንል ስህተት አይሆንም። ይህችን የብዙ ሰማእታት የደም ቀን በየአመቱ ዘክረነው ስንውል በልበ ህሊና የሚታየን ከውጭ የመጣ ጠላት አገራችንን ቀምቶ በቅኝ ግዛት ስር ለማስቀመት ባካሄደው ጦርነት እና ይህን ቀን በወለደው አመጽ ምክንያት ለሦስት ቀናት በፋሽት የጣሊያን ጦር ሰራዊት የወደመው ንብረት እና የተቀሰፈው የሰው ህይወት ነው።

የዚህች አሰቃቂ የፍጅት ቀን ግን ለአንዴም ለመጨረሻ ቆርጠኝነትን እና ለጠላት ያለማደርን ብርቱ እምነት በህዝብ ልቦና የሰነቀረበት ቀን ሆኖ አለፈ። ደም የጠማው የውጭ ወራሪ ከቤታቸው ያልወጡ ንጹህንን ደማቸውን አፈሰሰ። በእሳት አቃጠለ። ፍጹም እርህራሄ ቢስ የጠላትነት መልኩን ያለመደበቅ አሳየ።

በአንጻሩ ይህች ቀን ያልበገሬ ቃለመሀላን ያስገባች እና የጠላትን በአገር የመቆየት እድሜ ያሳጠረች ቀን ሆና አለፈች። ከሁሉም በላይ አገር፤ ሰንደቃላማና ቃል ኪዳን ለአንድ ክልል ወይን ለአንድ ቋንቋ የተተወ እንዳልሆነ የተመሰከረበት ቀን ነው። አወ የጣሊያን ፋሽስቶች የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በሀይል እና በግፍ ሰብረው፤ የህዝቡን በነጻነት የመኖር መብት ተዳፍረው ሲገቡ እንደ ዘዴ የተጠቀሙበት ወያኔ የተባለ የባንዳ ውላጅ እንዳደረገው ወይንም እያረገ እንዳለው ሕዝብን በቋንቋ እና በሀይማኖት የመለያየት እርኩስ ተንኮል ነበር። የሌባ ጣታቸውን የቀሰሩትም በአንድ ቋንቋ እና በአንድ የእምነት ቤት ነበር። ኦርቶዶክስና አማራ የሚለው የዘመኑ የጠባብ መንደርተኞች ፍልስፍና የተፈጠረውም ዛሬ በወያኔ ሳይሆን ያኔ በፋሽስቱ የጣልያን ወራሪ ሀይል ነበር።

ይህን አስመልክቶ የተከበሩ አርበኛው እና ስመጥሩ ደራሲ ክቡር ሐዲስ አለማየሁ ትዝታ በተሰኘው መጽሀፋቸው የጠላትን ወረራ እና እርሳቸው ተሰልፈውበት የነበረውን የጦር ግንባር በተመለከተ ለትውልድ ሲነግሩን፤ ክቡር ለዑል እራስ እምሩ በሽሬ የጦር ግንባር በተደረገው የመከላከል ውጊያ ሰራዊታቸው በመርዝ ጭስ በአውላላ ሜዳ ሲነድ በማየታቸው ከጦር አበጋዞቻቸው ከመከሩ በኋላ ውጊያውን ወደ ምእራብ ኢትዮጵያ ማዞርና የተራዘመ የሽምቅ ትግል መጀመር በማለት ጦራቸውን ሳይፈቱ ወደ ጎሬ ሲጓዙ።

ወጣቱን አርበኛ ሀዲስ አለማየሁን ወደሱዳን ልከው መድሀኒት፣ ትጥቅና ስንቅ ይዘው እንዲያልፉ አደረጉ። ልዑል እራስ እምሩም ጎሬ ደርሰው ከዘመቻ በፊት በተመከረውና የአገሪቱ እንደራሴ እና የዘውዱ ጠባቂነት ስልጣን ከተሰጣቸው ከቢትወደድ ወልደጻድቅ ጋር በመሆን የነጻነቱን ትግል ማስቀጠል ይቻላል በማለት ነበር የተጓዙት። በተጨማሪም በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ በኩል የእራስ ደስታ ዳምጠው እና የደጃዝማች በየነ መርእድ ጦር ያልተፈታ በመሆኑ፤ የወለጋው ገዥ ደጃዝማች ሐብጠማሪያም ገ/እግዚአብሄር ከሙሉ ሰራዊታቸው ጋር በአገራቸው መኖራቸውን ስለታወቀ ከነዚህ ሁሉ ተባብሮ ጠላትን ከገላጣው የሰሜን ተራሮች ይልቅ ጫካ የበዛበቱ የምእርብ ኢትዮጵያ ለትግሉ ጠቃሚ መሆኑ ታምኖበት ስለነበር። የእራስ እምሩም ከሙሉ ሰራዊታቸው ጋር ጉዞ ይህን ለማሟላት ቢሆንም ጎሬ ከደረሱ በኋላ ግን የቢትወደድ ወልደጻድቅ አቋም ሳይስማማቸው በመቅረቱ ሰራዊታቸውን ይዘው ወደወለጋ ገሰገሱ። የወለጋው ገዥ ከጠላት ጋር በመስማማት ሰራዊት ልከው ለአገሩ እና ለነጻነቱ ሲል ከአገር አገር በመንከራተት ላይ የነበረውን የእራስ እምሩን ጦር በታህሳስ 1929 በድንገት አስከብበው ብዙ ሰው እንዲያልቅ ሆነ።

ክህደት በዚህ ሳአያቆም ወደጅማ የተደረገውም ጉዞ እንዲሁ በአባጆቢር ምክንያት እንዳልተሳካ እና ሰራዊቱ አቅጣጫውን ቀይሮ ወደከፋ በሚጓዝበት ግዜ ጎጅብ ወንዝ ላይ በባንዳ መሪና ጥቆማ የታገዘው የኮሎኔል ማልታ ጦር የእራስ እምሩን ጦር በመክንበብ ከነሰራዊታቸው። የጅማውን ከንቲባ ጋሻው ጠናን እስከ ጦራቸው እንዲሁም የኢትዮጵያ የዘመናዊ ጦር እርሾ የነበሩትን የወለታ ስልጡን ወታደሮች ጭምር በጠላት እጅ ወደቁ።

ኮሎኔል ማልታ በዚህ ሳያበቃ ከውጊያ ይልቅ ድለላን እና የእርስ በእርስ ማናከስን የጠላት ዘዴ በመጠቀም በታህሳስና የጥር ወራት እራስ ደስታንና ቢትወደድ በየነ መርእድንም ሰራዊት ፈታ። የተከበሩትን አርበኛና መስፍን እራስደስታንም አሰቃቂ ወንጀል ተፈጸመባቸው። የጠላታችን የ 1888 የአድዋ ውድቀታቸውን እና ሀፍረታቸውን ለመበቀል በተለያየ መልክ በመላ አገራችን ገሚሶቹ በቁስነት ስም ሌሎቹ በተመራማሪነትና በዲፕሎማትነት በመምጣት፤ የአገራችንን የዚያን ዘመን ገዥወች፤ የነጭ ለባሾችንና ያጥቢያ ዳኛን ሳይቀር በወዳጅነት በመያዝ አልፎ ተርፎም እስከ ጡት መጣባት ዝምድና የደረሱበት ሁኔታ ነበር።

ለዚህም ነበር የመጀመሪያዋ የጠላት አብሪ ጥይት ስትተኮስ የትግራዩ ገዥና የንጉሡ ነገስቱ የልጅ ባል የነበረው ኃይለስላሴ ጉግሳ እስከ ስራዊቱ ለጀኔራል ዲቦኖ ያደረው። አገሩንም በመንገድ መሪነትና በሹንባሽነት ወጋ አስወጋ።

## የካቲት 12 1929

ከላይ እንዳሰፈርሁት የፋሽስቱ የጣሊያን ተወካይ ግራዚያኒ በዚህች ቀን ፌሽታውን በአንድ የልዑል መወለድን ምክንያት ቢያደርግም፡ ዋና ጉዳዩ አዲስ አበባን ከያዙ በኋላ በሁለቱ ልኡላን እራሶች (እምሩ ኃይለስላሴ፣ ደስታ ዳምጠው) እና በሁለቱ ደጃዝማቾች (በየነ መርእድ፣እና ገብረማሪያም) የቀጠለው (resistance )እና በሀምሌ 1928 አዲሳበባን መልሶ ከጠላት ለመንጠቅ በአርበኞች በእነ እራስ አበበ አረጋይ ተሞክሮ የከሸፈው (በዚያች እለት አቡነ ጴጥሮስ በጠላት እጅ ወደቁ) እና  የተመኟት አገራችን ሙሉ በሙሉ በእጃችን ገባች በማለት በደስታ ፈንድቀው ለድሆች ምጽዋት ለመስጠት እና ቀኑን በፌስታ አክብሮ ለመዋል በባንዳነት የገቡለትን የአገሪቱ ታላላቅ ሰወች እነ እጌታቸው አባተ፣ እራስ ኃይሉ ተክለ ሀይማኖት፣ እራስ ስዩም መንገሻ እና ግብጻዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባት የሆኑት አቡነ ቄርሎስ በተገኙበት የፋሽስቱ የማርሻል ግራዚያኒ ስነስርአት ተጀመረ።

በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በግዜው ብዙ አባቶች ወራሪውን ያልተቀበሉና ከህዝቡና ከአገር ነጻነቱ ጎራ የወገኑ ቢሆንም ለ 1900 አመታት እንደቆየው የቤተክርስቲያኗ ስርአት በአሌክሳንደሪያ ሲኖዶስ ስር ሊቀጳጳሱም ከዚያ በሚመጡ አባቶች ስትተዳደር እስከ 1945 ኖራለች (ዲያቆን ዳነኤል ክብረት የቤተክርስቲያን መረጃወች)። በመሆኑም እንደሚገመተው ጠላት አገሪቱን በወረረበት ወቅት ሁለቱ ታላላቅ አባቶች አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል እብሪተኛውን ህዝብ እንዳይገዛለት አውግዘው ከኢትዮጵያ አርበኞች ጎን በመቆም መስዋእት ሲሆኑ።

ከውጭ የመጡት ሊቀጳጳስ ለጠላት አድረዋል። ማስረጃ በሌለው እንደሚወራውም ቤተክርስቲያኗን በፍጹም የበላይነት እርሳቸው እንዲረከቡ ግራዚያኒን ጠይቀው አልተሳካላቸውም ይባላል።

ያም ሆነ ይህ በዚህ የፋሽስት ደስታ ቀን በክብር ከተጠሩትና የመቁሰል አደጋ ከደረሰባቸው አንዱ ሲሆኑ የእርሳቸውን ጥል ያዥ የነበረው ሰው ግን ወዲያዉኑ ሞቷል። በሁለቱ ወጣት አርበኞች ተከታትሎ በተወረወረው የቦንብ ጥይቶች የቆሰሉት ቁጥር ቀላል ባይሆንም በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት እንደተዘገበው ቁጥራቸው ቀላል የምይባል መኳንንቶችና መሳፍንቶች በዚሁ ቀን ታማኝነታቸውን ለመግለጽና ለፋሽስቱ መንግስት ተገዝነታቸውን ለማስመስከር በዚሁ በትንሹ ግቢ ተገኝተዋል።

ግራዚያኒም በእብሪትና በኩራት ድስኩር በማንበብ ላይ እንዳለም ቁጥረ ብዙ የእጅ ቦንቦች ተወረወሩበት። እርሱን ጨምሮ የእርሱ ምክትል አርማንዶ ፒትሬቲ፣እና የአየር ሀይሉ አዛዥ ጀኔራል ላይኦታ ቆስለው ወደሆስፒታል ሄደዋል። ኢትዮጵያን በመርዝ ጭስ ያቃጠለው የአየር ሀይል አዛዥ እግሩ እስከመቆረጥ ደርሷል።

በዚህች የየካቲት ቀን ፋሽስቶች ለደስታና ውካታ ሲዘጋጁ የአገር ፍቅር ያንገበግባቸው የነበሩት ሁለት ወጣት ጓደኛሞች ደስታውን ወደልቅሶ ለመቀየር ችለው ነበር። እነዚህ ወጣቶች አብረሀም ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶም በትውልድ ኤርትራውያን ሲሆኑ አገራችን ብለው መስዋእት የሆኑት በእርግጥም ለእናት አገራቸው ለኢትዮጵያና ለባለሦስት ቀለም ሰንደቃላማቸው ነበር።፡ይሕን ደግሞ አብርሐም ገና ከቤቱ ከመውጣቱ በፊት የጣሊያንን ባንዲራ ከወለል በማንጠፍ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በላዩ ላዩ በቆመ እንጨት አውለብልቦት እንደሄደ ታሪኩ ይነግረናል።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ሰሞኑን አቶ ተስፋየ ገብረአብ የተባለው ጸረ ኢትዮጵያ ግለሰብ ለፕሮፌሰር መሳይ ከበደ በተስማማበት (ባግባባቸው) (ባመሳሰላቸው) ስሁፍ ላይ ከዚህ በታች የሰፈረውን አስተያየት አስፍሯል። ፕሮፌሰሩ ምን አሉ ለሚለው ጉዳይ ስላልሆነ እዚህ ላይ አልሰፈረም።

---

"በአካባቢያችንም ሆነ በሌሎች ተንታኞች የሚፃፉ አስተያየቶችን ስናነብ ኢትዮጵያ መንታ መንገድ ላይ መቆሟን እንገነዘባለን። ይህም ከማይቀረው አንድ መተራመስ በሁዋላ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊት አገር ሆና በአስተማማኝ መሰረትላይ ቆማ ትቀጥላለች ፤ አሊያም መረራ ጉዲና አራተኛው ይሆናል (Scenario) ብሎ እንዳስቀመጠው ኢትዮጵያ በስብሳና ተንጣ እንደ ሃገር ትፈርሳ ለች። (መፍረስ ቢከሰት በፍርስራሹ ላይ ሌላ የአዲስ ታሪክ መሰረት እንደሚጀመርበአእምሮአችን መያዝ ይገባል።) እና መንታ

መንገዶቹ እነዚሁ ናቸው። ስለ ኢትዮጵያ መፍረስ ጉዳይ መናገር ክፉ በመመኘት አይደለም። አፍጥጦ እየመጣ ያለውን እውነት ከወዲሁ ማወቅ መፍትሄ ለመፈለግ ያግዛል በሚል ነው።ከመነሻው መሳይ ከበደ ኢትዮጵያን ከመፍረስ ሊያድኑ ከሚችሉ ልሂቃን አንዱ ሊሆን ይችላል ብዬ ተስፋ ያደረግሁባቸውን በር ከፋች አመለካከቶች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን በዚህ መጣጥፍ እያነሳሁ የ ግል አስተያየቴን አኖራለሁ።

አብርሀም ደቦጭም ሆነ ሞገስ አስገዶም የተስፋየ ገብረአብን ወይንም የመለስ ዜናዊን አለያም አሁን በስልጣን ላይ ያሉትን ሁሉ ዘረኞችና የፍርሻ ፊታውራሪ ወይንም ምኞተኞች ያክል በኢትዮጵያ ኖረው አልተጠቀሙም። ግን የአገር ፍቅርን። የኢትዮጵያን ተንሳኤ ከእነርሱ ህይወት ባለፈ እና በዘለቀ አምነው የዚያችን ቀን የአርበኝነት ተግባር ፈጽመዋል። በመሆኑም ታሪክ ከዚያች ሁለት ነገሮች ከተደባለቁባት ቀን ጋር ሲዘክራቸው ይኖራል።

እንደተስፋየ ገብረአብም ሆነ እኔ አውቃለሁ ባይ ግለሰቦች ኢትዮጵያ እንደሀገር ለሦስት ሚሊኒየም ስትዘልቅ ብዙ የከፉ ቀኖችን አሳልፋለች። ከከፉት ዘመናት አንዱ እነ አብርሀም ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶም መስዋእት የሆኑበት በሦስት ቀንና ሌሊት 30 ሽህ የአዲስ አበባ ነዋሪ በአካፋ እና በዶማ። በጥይት እና በቤንዚን ከቤቱ ሳይወጣ የተቃጠለበት ዘመንን ይጨምራል። እኛም ይህችን የየካቲት ቀን ለሰማእታቱ በጸሎት ዘክረን እንውላለን። ጀኔራል ቦዶሊዮ አዲስ አበባ ሲገባ በግዚያዊ ድል አድራጊነቱ ተኩራርቶ "La fine della nazione Etiope" ይህ ምኞት ነበር።

ልክ እንደ ተስፋየ ገብረአብ ኢትዮጵያ አትኖርም ትጠፋለች የማለት ብቻ ሳይሆን ቦዶሊዮ የሚኒሊክን አልጋ በእጁ በመያዙ የጠፋች መስሎት አለቀላት አለ። የጣሊያን ፋሽስቶች ከመሰል የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ተባባሪወቻቸው ጋር ሆነው የኦሬንታል ጣሊአይንን አዲስ ግዛት የኢትዮጵያን ስም በመሰረዝ ተቀብለውት ነበር።

ሆኖም የኢትዮጵያ ተንሳኤ ግን አዲስ ከየካቲት 12 ፍጅት ማግስት ጀመረ። በ 30 ሽህወች ደም አገር ነጻነቷን ለማወጅ አርበኞቿ በዱር በገደል ላይመለሱ ቃል ገብተው ተፈጸሙ። ጣሊያንም በመጣበት መንገድ ሳይሆን እንደጉም ነው የበነነው። በኢትዮጵያ የነበረው የጥፋት ዘመቻ በአምስት አመታት ውስጥ ለፋሽስት ወራሪ ቀቢጸ ተስፋ ነው የሆነው።

ኢትዮጵያ ከዚያም የከፉ ዘመናት አሳልፋለች። በአንድ ወቅት በውስጥና በውጭ ጠላት መወጠር የዘመነ መሳፍንት የ 60 አመት ማህከላዊነት የሌለበትም ሁኔታ ተፈጥሯል። በየጊዜው ኢቶጵያ ከውድቀት ስትነሳ ግን አይላና እንደ እሳተ ጎመራ ጠላቶቿን ለብልባ ወይም አቃጥላ ትቆማለች። የበለጠ ጥንካሬና ሀያልም ትሆናለች። ይህ እውነት የሆነ ነው።

ዛሬ ወያኔ የሚሉት ወይንም ገንጣይ አስገንጣይ እንደምንለው ማለት ነው እኛ አፍርሰናታል ብለው እንደሚያስቡት ዘላቂነት የለውም ለማለት ነው።

ወደ የካቲት 12 ታሪካዊ ቀን ስንመለስ በሌላ በኩል የአገራቸው እና የሕዝባቸው ነጻነት ያንገበገባቸው ሁለት ወጣቶች አብርሀም ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶም የተባሉ። ትውልዳቸው በኤርትራ ይሁን እንጅ አገራቸው ኢትዮጵያ መሆኗን ነጋሪ ሳያስፈልጋቸው ይህንን የጠላት ፈንጠዝያ ዝግጅት ለመለወጥ ብሎም የአገር ፍቅርን እና የኢትዮጵያዊ አይበገሬነትን ለማሳየት ቆርጠው ተግባራዊ አድርገዋል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!

